Tsegaye Mamo et al		FSC

የወ/ይ/መ/ቁ.9862

ሚያዝያ 3 ቀን 1995ዓ.ም

ዳኞች፣- መቅደስ ተስፋዬ

ተገኔ ጌታነህ

አሰግድ ጋሻው

ይግባኝ ባይ፣- ልዩ ዐቃቤ ሕግ

መልስ ሰጪዎች፣- 1. ፀጋዬ ማሞ

2. ፍሬው መርሻ

3. በትረዮሐንስ ገብረሚካኤል

4. ተሾመ ተክሌ

መዝገቡን መርምረን ትዕዛዝ ሰጥተናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የልዩ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ ይዘት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ መልስ ሰጪዎች እንደቅደም ተከተላቸው በአስራ ስድስት፣ በአስራ ስድስት እና በአስራ ሰባት ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጡ የተወሰነባቸው የሚያከብዱ ነጥቦች ባሉበት ሁኔታ ስለሆነ ቅጣቱ ተሻሽሎ ከፍ ያለ ተመጣጣኝ ቅጣት ይወሰንባቸው፡፡ አራተኛ መልስ ሰጪን በተመለከተም ያቀረብነው ማስረጃ ክሱን በበቂ መጠን የሚያረጋግጥበት ሆኖ ሣለ ሣይከላከል በነፃ እንዲሰናበት የተሰጠው ብይን ተሽሮ እንዲከላከል ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

በኛም በኩል የስር ፍ/ቤትን መዝገብ ከይግባኝ ማመልከቻውና ከሕጉ ጋር እንዳየነው ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የተጠቀሱት መልስ ሰጪዎች ላይ የተወሰነባቸው ቅጣት የሚያንስ ሆኖ ስላላገኘነው በነዚህ ሦስቱ መልስ ሰጪዎች ላይ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ይግባኝ አልተቀበልነውም፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
... ግልባጭ
ፊርማ ... ቀን 25/05/96

አራተኛ መልስ ሰጪ ተሾመ ተክሌ ግን ክሱን መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት የተሰጠው ብይን ባግባብ መሆን አለመሆኑን /ብቻ/ ለመመርመር ብቻ ይግባኝ ያስቀርባል ብለናል።

ስለዚህ ልዩ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ ማመልከቻውን ከመጥሪያ ጋር ለአራተኛ መልስ ሰጪ ለተሾመ ተክሌ ያድርስለት፣

መልሱን ለመጠባበቅ ለግንቦት 1 ቀን 1995ዓ.ም ተቀጠረ።

የዳኞች ፊርማ፣ መቅደስ ተስፋዬ

ተገኔ ጌታነህ

አሰግድ ጋሻው

/አ.ገ/